International Association of Lasta Lalibela

We rise by lifting others.

Lastalalibela2024iall@gmail.com

https://ialastalalibela.org/

ታህሳስ 28/2017 ዓ.ም

ለመላው ኢትዮጵያንና ትውልደ ኢትዮጵያን በሙሉ

እንኳን ለጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ !

እንደሚታወቀው በሰሜን ወሎ ዞን ላስታ ላሊበላ ቡግና አካባቢ ህጻናትን ጨምሮ እናቶችና አዋቂዎች በከፍተኛ የምግብ እጥረት እየተጎዱ መሆኑን የአለም አቀፍ ሚዲያ መዘገብ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የላስታ ላሊበላ አለማ ዓቀፍ ማህበር በዋሽንግተን ዲሲ በልማት ማህበር እውቅና ያገኘና የምዝገባ ፈቃድ ያለው ሲሆን በለንደን ከሚገኘው የዛጉዌ ማህበር፣ የላስታ ላሊበላ ማህበረ ቅዱሳን ማእከል ጽ/ቤት እንዲሁም የቅዱስ ላሊበላ ልማት ማህበር/ላልማ/ ጋር  በመተባበር የእርዳታ ማሰባሰብ ተግባር ጀምሯል።

በእኛ ማህበር ለሚሰራው የሃብት ማሰባሰብ ሂደት ሞያዊ ድጋፍና የሚዲያ ሽፋን እየሰጣችሁን ያላችሁና ልትሰጡን በዝግጅት ላይ ያላችሁትን ሁሉ እናመሰግናለን። ከማህበራችን ጋር በጋራ ወጥነት ያለውን የችግሩን ጥልቀት ታሳቢ ባደረገና የተቸገሩትን ተደራሽነት ባገናዘበና ሃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው ስራ ለምሰራት ትብብራችሁንና አወንታዊ መልስ ለሰጣችሁን ሁሉ ከታላቅ አክብሮት ጋር በላስታ ላሊበላና ቡግና አካባቢ በረሃብ የተጎዱ  ህጻናትና እናቶች ስም እናመሰግናለን።

የማህበሩ ቦርድ ዋና ጸሃፊ መምህር አባ ጽጌስላሴ መዝገቡንና ዋና ሰብሳቢ መቶ አለቃ አያልሰው ደስዬን ያካተተ የማህበሩን ስራ አስፈጻሚዎች ለሚዲያዎች ከማሳወቅ ጀምሮ እስከ ስራው ፍጻሜ የሚከታተል ቡድን እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። በተናጠልና በማህበር የሚሰሩ ስራዎችን ማህበረሰቡን ከመደገፍና ለችግሩ አፋጣኝ መልስ ከመስጠት የመነጨና በቀናነት የመሆኑን ያክል ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ከሚያደናግሩና በማህበረሰባችን ስም ያልተገባ ጥቅም ፈላጊዎች በመጠንቀቅ ተጠያቂነትና ህጋዊነት ያላቸውን ማህበራትና ድርጅቶችን በመጠቀም ሃላፊነታችሁን ትወጡ ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን።

በዓሉን ስታከብሩ በረሃብና በችግር ውስጥ ያሉ ህጻናትና እናቶችን እያሰባችሁና እየደገፋችሁ ይሆን ዘንድ በፈጣሪ ስም እንጠይቃለን !

መልካም የልደት በዓል !

የላስታ ላሊበላ አለማቀፍ ማህበር

International Association of Lasta Lalibela (IALL)

620 Kennedy St NW, Washington, DC 20011